# “ያልሰለጠኑ አሰልጣኞች”

የጐንቻው!

‘ዋሻ ዘግተው’፤ ‘በዘር ቅኔ ደብትረው’ ደደቢት በድድብና ያደቆኑ፤
ብሔራዊ ካባ ቀደው የመንደር ቡትቶ ‘ውራጅ ጥብቆ’ የተጫኑ፤
ጥፋት፤ ድግምት ያጠነጠኑ፤ ‘በአበሻ ለምድ’፤ኮፈዳ ጣር፤ መከራ የለመኑ፤
ስር ቆፈረው፤ ቅጠል ቆርጠው፤ ‘እጸ-በለስ’ ቆርጥመው የማሰኑ፤
አሥራ - አሥር ዓመት ድሪቶ እየጠቀሙ እርቃናቸውን የመነኑ፤
የሃገር፤ የትውልድና የዘመን ጭንጋፎች ከጽንሳቸው የመከኑ፤
በክፉ እርግማን በአጥፎቶ መጥፋት የተካኑ፤
ዶክተር፤ ፕሮፌሰሮችን ‘እነ በረከት’ ‘ያልሰለጠኑት ሲያስለጥኑ’፤
**ተጠይቀው መልስ አልባዎች፤ አልቦ ባልቦ፤ ከምርጫ ውጭ ይከወኑ።**

‘ዓለም - በቃኝ’ በጨለማ ‘ጫጭተው - ጃጅተው’ የወየኑ፤
እውቀት፤ ብርይን፤ ራዕይ የታወሩ ዓይን አውጣዎች የዘመኑ፤
‘ቀንና ጸሃይ ሲወጣላቸው’ እንደ ሌሊት ወፍ ከእንቅልፋቸው የባነኑ፤
ተንጠራርተው፤ ተጠራርተው ጣራ፤ መንበር፤ ግንባር ተፎጥጠው የሚያበግኑ፤
በመንደር ድንኳን፤ሱቅ በደረቴ፤በኮንቴይነር ‘መሰረተ-ትምህርት’ ገና ‘ሀ ሁ’ን ያጠኑ፤
አቡጊዳን ሳይዘልቁ ‘ማስተር፤ ዶክተር’ ‘ወረቅቶች ውጭ ሸምተው ያቀኑ’፤
የፍልስፍና፤የፓለቲካ ፕሮፌሰሩን፤ ‘ሽመልስና ሬድዋን’ ስልጠና አቡክተው ሲያቀጥኑ፤
‘ከእጅ፤እጅ’ አልፎ፤‘እግር፤እግር’፤ ‘ቋቅ እሚያሰኝ’፤በአደባባይ ‘ያልሰለጠኑት ሲያሰለጥኑ’፤
**ጨዋታው አልቋል፤ ከሜዳ ይውጡ፤ እንደ ጉም፤ እንደ ደመናም ከላያችን ይበተኑ።**

በበረሃ ‘የራስ ቅላቸውን ያጠኸኑ’፤ ‘የአዕምሮ ዘይታቸውን ያተነኑ’፤
ደመነፍሳቸውን ‘ያልሰለጠኑት አሰልጣኞች’ በድርቅና ሲጀነኑ፤
‘ያልገባቸው - ሊያስረዱ’፤ ‘የማያውቁ - ሊያሳውቁ’ ብዙ በከንቱ የባከኑ፤
መንጋ ደናቁርቶች ያለፉ፤ የበቁ ምሁራንን ‘አጀዝበው’ ሲፈትኑ፤
ሃያ ዓመት ሙሉ ‘ዶማዎች’ አደደቡን ‘ያልሰለጠኑት ሲያሰለጥኑ’፤
**ካሁን ወዲያ እያወቅን ‘እንድንማማር’ ወያኔዎች መዳኛቸውን ‘አቅሰሰው እንድያጠኑ’።**

ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ መስፈርቱ ‘ልስጠና’ በታጠቁ ብረት አጣና፤
ለባለ ዲግሪዎች ድንጋይ ጠረባ ‘ድህረ-ምረቃ’ ‘ዶማ’ ፈተና፤
ሰብስቦ ምሁር፤ ሊቃውንት በአደራሽ የሚያስፋፉ ድንቁርና፤
መማር አያዉቁ መማማር፤ ሁሌ ‘አምስትዮሽ ጥርነፋ ገመና’
ዘንድሮ አያልፉም፤ አይኖርምምና ብሄራዊ ምርጫ ቀጠና፤
አገር አ‘ግቶ፤ ሕዝብ አጉላልቶ ኲሮጀ ዝርፊያ 99 ትርፍ ሲያቀና
ሕዝብ በተራው ሊማር- ሊማማር አ‘ብሮ-ጽንቶ ዘብ ይቆምና፤
እንድያሳይ፤ እንደመራም፤ የሻቱትን የምህረቱን ጉዳና፤
አለዚያም ይግቡ ደደቢት ‘ገዳማቸው’ ዳግም ካሰኛቸው ውይንና፤
እድሜ ልካቸውን እንዲማሩ ባደቆናቸው ዘር - ማይምና፤
እንደ ማቱ ሳላ ‘ሺህ ዓመት’ ንስሃ ገብተው ‘እስኪበቁ ለቅስና’፤
ሕዝብ ነቅቷል- ‘ደግሷልም’ ሊያስመርቃቸው በጡረታ ‘ዱፍትርና’፤
**በቃ ብሏል መደናቆር በኢትዮጵያ ባልሰለጠኑት ስልጠና።**

የጐንቻው! yegonchaw@yahoo.co.uk

# ማስታዋሻ፡-

---

*በዘመነ ወያኔ ‘ባልሰለጠኑ አሰላጣኞች’ ስልጠና ‘ከእጅ-እጅ አልፎ እግር-እግር ብሏቸው የስብሰባ አዳራሹንና ሰብሳቢዎቻቸውን ተጸይፈው አደባባይ በመውጣት ቁጣቸውን በድፈረትና በቆራጥነት ለገለጹ፤መስዋዕትነትም ለከፈሉ ወጣት ወገኖቻችን ምስጋናና መታሰቢያም ትሆን ዘንድ።*

*ጥር 2, 2007፣ (ጃንዋሪ 9, 2015)*